02

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር / Ref.No 4-0/44/10
ቀን / Date 22 ሚያዚያ 2010

ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
**አዲስ አበባ**

የተባበሩት መንግስታት የህፃናት መርጃ ድርጅት (UNICEF) በቁጥር OG/hl/116/18 እ.ኤ.አ 2/4/2018 በተፃፈ ደብዳቤ ድርጅቱ አገር አቀፍ የልማት ኘሮግራሞችን ለማስፈፀም የተለያዩ እቃዎች ከውጭ አገር በሚያስመጣበት ጊዜ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት እስከሚጠናቀቅ ድረስ ከወደብ ቀጥታ ወደ ቦንድድ መጋዘን ለማስገባት በግዴታ ደብዳቤ ሲስተናገዱ እንደነበርና አሁን ሲስተሙ ከASCUDA++ ወደ ECMS በመቀየሩ ምክንያት ድርጅቱ ቦንድድ መጋዘን መጠቀም አለመቻሉንና ሌሎችም ችግሮች እየገጠሙት እንዳለ በመግለጽ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በፃፈው የድጋፍ ደብዳቤ መሠረት በተፈቀደው ቦንድድ መጋዘን ለመጠቀም ዘላቂ መፍትሄ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡

በዚሁ መሠረት በቁጥር የ.ተ.መ.2/2/202 መጋቢት 29 ቀን 2008 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በሁሉም ክልሎችና በፌደራል መ/ቤቶች ለሚካሄዱ የተለያዩ ኘሮግራሞች በተለይ የጤና፣የውሃ፣የትምህርት መሳሪያዎችና ሌሎች ኘሮግራም ለማካድ የሚያገለግሉ መድሃኒቶች፣የውሃ ጉድጓድ መቆፈሪያ ማሽነሪዎች፣ የትምህርት መሳሪያዎችና የተለያዩ ቁሳቁሶች ከውጭ አገር የሚያስመጣ ድርጅት ስለሆነ ጊዜያዊ የመጋዘን ፈቃድ እንዲታደስ፣ወደፊትም በተፈለገ ጊዜ እድሳት እንዲደረግለት ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የገለጸ ከመሆኑም በተጨማሪ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በቁጥር አ7/12/49/128 ህዳር 24 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ እቃዎቹን በግዴታ ደብዳቤ ማውጣት እንዲችሉ በተጠየቀው መሠረት እንዲሁም በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ 118/1 ላይም የመንግስት ባለበጀት መ/ቤቶች በግዴታ ደብዳቤ መገልገል እንደሚችሉ የሚገልጽ ቢሆንም ዩኑሴፍ የሚያስመጣቸው ዕቃዎች ከወደብ ከመነሳታቸው በፊት ለየትኛው የመንግስት አካል እንደሆነ ስለማይታወቅ እቃዎቹ ዩኑሴፍ በሚያቀርበው የግዴታ ደብዳቤ መሠረት በIM7 ዲክላራሲዮን ተሞልቶና ዝርዝር ፍተሻ ተከናውኖ ለጊዜው ወደ ቦንድድ መጋዘን እንዲያስገቡ እንዲደረግ እየገለጽን በቀጣይ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የግዴታ ደብዳቤ ማቅረብ እንዳለባቸው አውቀው እንዲያከናውኑ ግልባጭ የተመዘገበላቸው

መሆኑን እያስገነዘብን ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የፃፈው 02 ገጽ ደብዳቤ፣የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የፃፈው 01 ገጽ ደብዳቤ፣የድርጅቱን ማመልከቻ 02 ገጽ እና የግዴታ ደብዳቤ 01 ገጽ በድምሩ 06 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አያይዘን የላክን መሆኑን እየገለጽን በዚሁ መሠረት እንዲፈፀም እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ተስፋዬ ቱሉ መልካ
ጉምሩክ ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር

<u>ግልባጭ</u>

- ለጉምሩክ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ኦፕሬሽን ድጋፍ ክትትል ቡድን
  <u>ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን</u>
- ለጅቡት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
  <u>ጅቡቲ</u>
- ለተባበሩት መንግስታት የህፃናት መርጃ ድርጅት (UNICEF)
  <u>ባሉበት</u>

Ethiopia Country Office
P.O. Box 1169
Addis Ababa, Ethiopia

Facsimile 251-11 551 711
251-11 551 1628
www.unicef.org

22/1224
25/07/10

Date: 2 April 2018
Ref no. OG/HL/110/18

Mr. Gaym Yibrah
Customs Procedure and Development Directorate Director
Ethiopian Revenue and Customs Authority Head quarter
Addis Ababa

Subject: Request for facilitation of ECMS system to accommodate UNICEF Shipments

Dear Mr. Gaym,

The United Nations Children's Fund (UNICEF) in Ethiopia has the honor to provide this letter to Ethiopian Revenue and Customs Authority, Head office and inform the following.

UNICEF imports different types of Pharmaceuticals, Nutrition products, education materials, water and sanitation supplies and vehicles for various government institutions in all regions of the country as part of UNICEF's program assistance to the development plan of Ethiopia and as part of emergency intervention. Imported supplies directly moves from the port to Bonded warehouse until the custom clearance formalities are finalized with a letter of undertaking. These helped UNICEF and it government partners to avoid paying unnecessary cost of demurrage/storage at the ports and getting the supplies on a timely manner.

Due to ERCA's new move from ASYCUDA ++ to the web based customs declaration system, UNICEF is unable to use its bonded warehouse privilege that worked well for the interest of all stake holders in the past. UNICEF is unable to register incoming shipments with declaration number for transit permit purpose with the new system (ECMS) . The issues faced with the introduction of ECMS are:

1. Non-existence of registration of a declaration for transit permit request purpose (specially permitted privilege for UNICEF)
2. Delay, financial, time and product quality and expiry consequence to fulfill all the required to access and submit to declaration to ERCA

We would like as well to remind the various previous correspondences related to our special bonded warehouse privilege and prior approvals and confirmations given to us to replace guarantees with undertaking letter. As you know these two are main considerations in finding viable solution for UNICEF and its partnering government ministries /offices to be able to continue existing privilege in the interest of all.

Ethiopian Revenues and ... Authority
Records & Doc...

Eastern and Southern Africa
6226789 622351
Regional Office
P.O. Box 44145
Nairobi, Kenya

Facsimile 254 2
www.unicef.org

This is therefore to kindly request your serious consideration of the matter and provides- solution to move our cargos stranded in Djibouti since the introduction of ECMS on March 2018 including the way forward in finding viable solution. We also kindly request you to provide us permanent solution to our bonded warehouse permit based on the attached support letter issued by MoFEC (attached here with) for your easy reference.

The United Nations children fund in Ethiopia avails itself to take this opportunity to express its appreciation and gratitude for your unreserved support and looks forwards to have a solution that allows UNICEF Ethiopia office to continue its support to Federal and regional governments.

Sincerely yours,

Regina Aplogan
Chief of Supply & Logistics

UNITED NATIONS unicef CHILDREN'S FUND

Encl: 2 pages

unicef | for every child

Date: April 9, 2018
Ref: LOG/MW/131/2018

Mr Gaym Yibrah
Customs Procedure and Development Directorate Director
Ethiopian Revenue and Customs Authority Head quarter
Addis Ababa

**Subject: Request to Use Letter of Undertaking approval and bonded warehouse permit/use for its operations.**

Dear Mr Gaym,

We refer to our letter dated April 02, 2018 with ref no.OG/HL/110/18 requesting your serious consideration to provide a solution to move our cargoes stranded at Djibouti port since the introduction of ECMS on March 2018 and to find a viable solution and permanent solution for our bonded warehouse permit.

We would like to bring to your kind attention that UNICEF used to import various aid shipments through undertakings based on requirements of government organizations. By having the bonded warehouse, UNICEF assists the beneficiary government partners to save foreign exchange payments due to port storage and container demurrage costs until the beneficiaries settle tax. the quality of supplies( particularly plumy nuts and pharmaceuticals) is also maintained by delivering the supplies on time. Transit permits had been issued till date with a mutual understanding with your good office of these situations without any problem.

Considering the time taken by the beneficiary government organizations to make arrangements for tax payments either through budget letters or tax free privileges, UNICEF Ethiopia kindly request your office to continue importing of the donated supplies as usual through undertaking and issue transit permit without paying tax.

The United Nations children fund in Ethiopia avails itself to take this opportunity to express its appreciation and gratitude for your unreserved support and looks forwards to the completion and application of your approval that allows UNICEF Ethiopia office to continue its support to Federal and regional governments.

Sincerely

Sirgut Mulatu
OIC, Chief, Supply and Procurement
UNICEF Ethiopia – Addis Ababa

እስካሁን ባለው አሠራርም የዩኒሴፍ ብቻ ሳይሆን ያዓለም ባንክና የሌሎች እርዳታ ሰጪ ተቋማት ዕቃዎችም ከውጭ እንደገቡ በዚህ መጋዘን በማከመቸት ወደሚመለከታቸው የፌደራል መ/ቤቶችና ወደ ሁሉም ክልሎች እንዲሠራጩ ለማድረግ ሲረዳ ቆይቷል:: በመሆኑም የዚህ መጋዘን መኖር በተለይ ቀደም ሲል አስፈላጊ ሠነዶች ተዘጋጅተውና ተፈርመው ስምምነት ለተደረሰባቸው እ.ኤ.አ. ከ2016-2020 በተ.መ. ተቋማት ድጋፍ ለሚካሄዱ አገር አቀፍ የትብብር ፕሮግራሞች መሳካት ወሳኝ ነው::

በመሆኑም የመጋዘኑ መኖር በለጋሽ ድርጅቶች ድጋፍ ለሚካሄዱ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች መሳካት ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳለው ታውቆ ለተቋሙ የመጋዘኑ ጊዜያዊ ፈቃድ እንዲታደስ፣ ወደፊትም በተፈለገ ጊዜ እድሳት እንዲደረግለት በእናንተ በኩል አስፈላጊው እንዲደረግ እናስታውቃለን::

ከሠላምታ ጋር

አብዱልአዚዝ መሐመድ

ሚኒስትር

